
# የእውነታ ሉህ ቁ. 7
# የዘር መለየት ድህነት በፍትህና ፖሊስ ጥበቃ

## በዘር የተለዩ ሰዎች በፍትህና በፖሊስ አያያዝ እንዴት ተጎድተዋል?

**(የዘር) መገለጫ**: እ.ኤ.አ. ከ2013 እስከ 2015 ድረስ የኦታዋ ፖሊስ አገልግሎት ጥቁሮች አሽከርካሪዎችን ከሚጠበቀው በላይ 2.3 ጊዜ ያህል ያስቆሟዋቸዋል፡፡
መኪና በሚያሽከረክር ሕዝብ ውስጥ የእያንዳንዱ ውክልና ቢታይ፣ ወጣት ጥቁር ወንዶችን ከ8.3 ጊዜ በላይ ሲያስቆሟቸው የመካከለኛው ምስራቅ ወንዶች አሽከርካሪዎችን ከ3.3 ጊዜ በላይ አስቁሞአቸዋል፡፡ እንዲሁም ወጣት የመካከለኛው ምስራቅ ወንዶችን 12 ጊዜ በላይ አስቁመዋቸዋል፡፡
**ቅድመ-ፍርድ እስራት**: በኦንታሪዮ ውስጥ በዋስ የፍርድ ስርዓት ስለ መለቀቅ በሚመለከት በ2016 የቀረበው ሪፖርት እንዳመለከተው ነባር የአገሬው ተወላጅ ሰዎች እና ባለ ቀለም ሰዎች "ከመጠን በላይ በሆነ የፖሊስ አያያዝ እና በዘር መገለጫ ማጥራት የሚቸገሩ ሲሆን ከችሎት ፍርድ በፊት ራሳቸውን እስርቤት የማግኘት ያላቸው ዕድል ከፍተኛ ነው፡፡

**መለያየት፡-** እ.ኤ.አ. በ2016 በቶሮንቶ ደቡብ እስርቤት ማእከል ውስጥ ቶሮንቶ ሜትሮፖሊታን ካሉት ብዛታቸው 7.5% ሆኖ እያለ በእስር ተለይተው ታጉረው የሚገኙ እስረኞች 40% ጥቁሮች ነበሩ፡፡
በብሔራዊ ደህንነት ጉዳይ ላይ የመንግሥት ዘገባዎች እንደሚያመለክቱት የአሸባሪነት ምንጭ ናቸው ብለው የሚቆጥሯቸውን እስላም ግለሰቦችና ድርጅቶች ላይ ያተኩራሉ፡፡

**- ይህን የሚያደርጉት በመላ ካናዳ ያሉትና ከዚህም በላይ የከፉ፣ ከ100 በላይ የቀኝ-ክንፍ የነጭ የበላይነት ስሜት አቀንቃኝ ቡድኖችና ከእነርሱ በኩል የሚመጡ ተጨባጭ ስጋቶችን ችላ በማለት ነው፡፡**



**የመታሠር መጠን**: ጥብቅ የፍተሻ ደረጃዎች ሁኔታ "ከነጭ ሰዎች ጋር ሲነፃፀር በቁጥር አነስተኛ የሆኑት (ባለቀለም) ሰዎች በቁጥጥር ስር የመዋል፣ በጥፋተኝነት የመፈረጅ እና የመቀጣት እድላቸው ከፍተኛ ነው"፤ ይህም በወንጀለኞች ፍርድ ቤት አደባባይ ተከሠው የሚመጡ ጥቁር ወንዶች በቁጥር ከመጠን በላይ ሆነው እንዲታዩ አስተዋጽኦ ማድረጉ ታውቆአል፡፡

**በቁጥጥር ሥር መሆን፡-** እ.ኤ.አ. በ2016 ጥቁሮች ከአጠቃላዩ የካናዳ ህዝብ ብዛት 3.5% የነበሩ ሲሆን በፌደራል ደረጃ ባሉት እሥርቤቶች ሲታዩ ግን 10% ያህል የያዙት እነሱ ነበሩ፡፡

## የአገሬው ተወላጆች ትኩረት

እ.ኤ.አ.ከ1980 እስከ 2012 ባለው ጊዜ መካከል በመላው ካናዳ ዙሪያ ወደ 1,200 የሚጠጉ የጠፉ ወይም የተገደሉ የአገሬው ተወላጅ ሴቶች መኖራቸውን ሮያል ካናዳ ማውንትድ ፖሊስ (RCMP) አምኖአል፡፡
የአገሬው ተወላጅ ሴቶች ቡድኖች ግን የጠፉትና የተገደሉት ቁጥር ከ4000 በላይ መሆናቸውን እንደዘገቡ ይገልጻል፡፡ በ2004 በተደረገው አጠቃላይ ማህበራዊ ጥናት መሠረት የአገሬው ተወላጅ ካልሆኑት ይልቅ ዕድሜያቸው 15 እና ከዚያ በላይ የሆኑ የአገሬው ተወላጅ ሴቶች ለዓመፅ የመጋለጥ እድላቸው 3.5 እጥፍ እንደነበረ ተመልክቶአል፡፡
እ.ኤ.አ. በ2016 የአገሬው ተወላጅ ሴቶች ግድያ ተወላጅ ካልሆኑ ሴቶች ይልቅ መጠኑ 5 ጊዜ ያህል ከፍ ያለ ነበር፡፡
በኦንታሪዮ እስር ቤቶች ከታጎሩት ውስጥ 14% የሚሆኑቱ የአገሬው ተወላጅ ሰዎች ናቸው፡፡ በ2016 (እ.አ.አ.) በእስር ለመታጎር ከሚዳረጉት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የአገሬው ተወላጅ ሴቶች እና ወንዶች ሆነው ራሳቸውን የመግደል አደጋ አዝማምያ ላይ እንደነበሩ ታውቋል፡፡
በአር ሲ ኤም ፒ (RCMP) ዘገባ መሠረት ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑት የህገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች የካናዳ ዜጎች ናቸው ፡፡ ከተጠቂዎችም ውስጥ 92% የሚሆኑት ለወሲባዊ መጠቀሚያ ዓላማዎች የተሸጡ ናቸው፡፡
በካናዳ ውስጥ አብዛኛው ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባዎች የሆኑት የአገሬው ተወላጅ ሰዎች ሲሆኑ ብዙዎቹ ወጣቶች ናቸው ፡፡
እ.ኤ.አ. በ2016 እስረኞች ከጠቅላላው የካናዳ ህዝብ ድምር 4.3% በመቶ ብቻ ቢሆንም በፌደራል ደረጃ የታሰሩ ሰዎች ብዛት 25% ሆኖ በፌደራል ደረጃ ፍርድ ከተፈረደባቸው ሴቶች መካከል 35% የሚሆኑት የአገሬው ተወላጅ ሴቶች ናቸው፡፡
እ.ኤ.አ. ከ 2005 እስከ 2015 ባለው ጊዜ ውስጥ በቁጥጥር ስር የዋሉት የአገሬው ተወላጆች አሃዝ ከ50% በላይ የጨመረ ሲሆን ፣ የታሰሩ የአገሬው ተወላጅ ሴቶች ቁጥር ግን ከዚሁ በእጥፍ አድጓል ፡፡

**ሥጋት**:  በዘር የተለዩ ማኅበረሰቦች ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ህዝብ መካከል ብዙዉን የሚወክሉ ሲሆን ለመኖሪያ ቤት እጦት፣ ለእስርቤት መታጎር እና ለሰብአዊ መብት ጥሰቶች ከፍተኛ ተጋላጭነት አላቸው፡፡
ይህ ለፍትህ እና ለህንነት ያላቸውን ተደራሽነት እያሽቆለቆለ ሄዶ ለፖሊስ ያልተመጣጠነ ክትትል የመጋለጥ እድላቸውን ከፍ ያደርገዋል፣
**ተደራሽነት**: ለፍትህ ችሎት፣ በዘር የተለዩ ግለሰቦች በፍርድ ቤት ችሎትና አስተዳደራዊ ችሎቶች በአግባብና በትክክለኛነት እንዲወከሉ፤ እንዲሁም በአንድ በኩል ባላቸው የዘር ልዩነትና የስደተኝነት ሁኔታ የሕግ ጠበቃ እርዳታ አያገኙም፤ በሌላ በኩልም እንደ ባህላቸውና ቋንቋቸው ዘንድ መልስ የሚሆናቸውን፣ ደህና የሆነ አገልግሎት የማግኘት ከፍተኛ የእጥረትና ችግር ያጋጥማቸዋል፡፡
**በወንጀለኝነት መፈረጅ፡** የካናዳ የዋስትና ስርዓት “ባልተመጣጠነ መንገድ ይቀጣል - ድህነትን፣ ሱሰኝነትን፣ የአዕምሮ ሕመምን ይወነጅላል”- በቀለም ኮድ የተጻፈውን ኢፍትሃዊነትን ያባብሳል፡፡

## ፈጣን ማስታወሻዎች

ስለ ባለ ቀለም ህዝቦች ስንነጋገር የዘር መሠረታችውና ቅሬተ-ቅርሳቸው ከአውሮፓ ያልሆኑትን ካናዳውያንን ማለታችን ነው፡፡ እነዚህም ካናዳ ውስጥ የተወለዱና ከካናዳ ውጭ የትም የተወለዱ፣ በሁለቱም ጎራ ስላሉ የቀለም ሰዎች መናገራችን ነው፡፡
ነባር የአገሬው ተወላጆች ስንል በአገሪቱ የነበሩ ቀድምት ህዝቦች {First Nations / Natives}  [የተመዘገቡና እውቅና የተሰጣቸው እንዲሁም ያልተመዘገቡ) ሜቲስ እና ኢንዩት ስለሚባሉ ሕዝቦች ነው፡፡
በቶሮንቶ ውስጥ በድህነት ከሚኖሩት ሰዎች ውስጥ 62% የሚሆኑቱ በዘር ልዩነት ከሚታዩ ቡድኖች የመጡ ናቸው፡፡
በካናዳም በዘር ልዩነት ከሚታዩት ውስጥ 52% የሚኖሩት በኦንታሪዮ ውስጥ ነው፡፡

በካናዳ ውስጥ በዝቅተኛ ገቢ ተቆራጭ (LICO) ወይም በዝቅተኛ የገቢ ልኬት (LIM) የሚመደቡ ቤተሰቦች ከገቢዎቻቸው ውስጥ በጣም ከመቶኛ ውስጥ ትልቁን የሚያጠፉት በአስፈላጊና መሠረታዊ ነገሮች ማለትም እንደ ምግብ እና መጠለያ የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ድህነትን የምንለካውም በዚህ መንገድ ነው፡፡
**ስልታዊ ዘረኝነት** ብዙዉን በስውር በሚሠራ ተቋማዊና የተዛባ ፖሊሲ፣ ልምምድና አሠራር ምክንያት የሚፈጸም ሆኖ በተለያዩ ቡድኖች መካከል አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ አሠራር ነው፡፡
የተወሰኑ ቡድኖችን በተለያዩ መንገዶች እንዴት ሊጎዳ እንደሚችል አስቀድሞ ግምት ውስጥ ያላስገባ፣ ሁልጊዜም እንደተለመደው አካሄድ ብቻ የመከተል ውጤት ሊሆን ይችላል፡፡

እ.ኤ.አ. በ2014 በካናዳ ውስጥ በአንድ የተወሰነ የዘር ቡድን ላይ በጥላቻ ተነሳሽነት የተፈጸሙ 611 ወንጀሎች (በዋነኝነት ጸረ-ጥቁር ዘረኝነት 238) ፤ እንዲሁም 429 ያህል ወንጀሎች በአንድ የተወሰነ የሃይማኖት ቡድን ላይ በጥላቻ ተነሳሽነት (በዋነኝነት አይሁዶች 213 እና እስላሞች 99) ተፈጽመዋል፡፡
በእስላሞች ላይ ያለው የጥላቻ ወንጀል በ2014 እና በ2016 መካከል በእጥፍ አድጓል፡፡
ሆኖም እነዚህ አኃዛዊ መረጃዎች ያልተሟሉ ናቸው፣ ምክንያቱም ሪፖርት የተደረጉ፣ በሥርዓት የተቀዱና ክትትል የተደረገባቸው ጥቂት የጥላቻ ድርጊቶች ብቻ ስለሆኑ ነው፡፡
በሌላ በኩልም እ.ኤ.አ. በ2013 የጥላቻ መልዕክቶችን ማስተላለፍ እንደ ወንጀል ተቆጥሮ ክስ እንዲቀርብበት የሚፈቅደውን የካናዳ የሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ሕግ ክፍል 13 በወግ-አጥባቂ መንግሥት ስለተሻረ ነው፡፡
በዚህም በካናዳ ውስጥ ጥላቻን ለመፍታት በሰብአዊ መብቶች አሠራር በኩል ይገኙ የነበሩትን መንገዶች ቀንሷል፡፡
እ.ኤ.አ. ከ2015 ጀምሮ ካናዳ ውስጥ ከተፈጸሙትና ሪፖርት ከቀረበባቸው የጥላቻ ወንጀሎች ውስጥ ቴንደር ቤይ፣ ኦንታሪዮ ከፍተኛውን ቁጥር ይዟል (ግማሽ የሚሆኑት በአገሬው ተወላጅ ሰዎች ላይ ያነጣጠሩ ናቸው)፡፡

# ምን እየተደረገ ነው?

**የአቦሪጂናል የሕግ አገልግሎቶች፡** ከመላው ኦንታሪዮ የሚመጡ የአገሬው ተወላጆችን (Indigenous) የመወከል ሙያዊ ክህሎትን ያዳበረ እና በካናዳ ትልቁ የአገሬው ተወላጆችን መርሃ ግብሮችን የሚያኖር አካል ነው፡፡
www.aboriginallegal.ca / info@aboriginallegal.ca

**የኦንታሪዮ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (OHRC)** ሥር የሠደዱና የተስፋፉ የአድልዎ መዋቅሮችና ሥርዓቶችን በማጋለጥ፣ በመመከትና እንዲያበቃላቸው በማድረግ፣ በትምህርት፣ በፖሊሲ እድገት፣ በሕዝባዊ ጥያቄዎች እና ሙግት ሰብአዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ ብሎም የተጠያቂነት ባህል እንዲፈጠር ይሠራል፡፡
www.ohrc.on,ca / info@ohrc.on.ca

**የእስላሞች ብሄራዊ ምክርቤት በካናዳ (MCCM)** ፀረ-እስላም፣ ጥላቻ እና አድልዎ የሚያጋጥማቸውን ሰዎች በመወከል ይሟገታል፡፡ እንዲሁም የፀረ-እስላም አድልዎ፣ ትንኮሳ ወይም የጥላቻ ወንጀል ሲሰነዘር በሰነዶች መዝግቦ ይይዛል፡፡
www.nccm.ca / info@nccm.ca